# ***የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት***

# ***መመሪያ ቁጥር 69/2004***

ግብር ከፋዮች የክፍያ ግዴታቸውን መወጣት እንዲችሉ ባለሥልጣኑ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ፣ድጋፍና እገዛ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ፣ በወጭና ገቢ ንግድ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች የሚፈለግባቸውን የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ በአንድ ጊዜ መክፈል በማይችሉበት ሁኔታ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የክፍያ ጊዜ ስምምነት በጊዜ የተገደበ፣ ግልፅና ተጠያቂነት ያለበት ሁሉንም ግብር ከፋይ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚያስተናግድበት የአሠራር ሥርዓት እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 112 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ይህንን የአፈፃፀም መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ***ምዕራፍ አንድ***

## ***ጠቅላላ ድንጋጌዎች***

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት" መመሪያ ቁጥር 69/2004 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር ለዚህ መመሪያ፣

1) ***"አስመጪ"*** ማለት ማናቸውም ገቢ ዕቃ ወደ ጉምሩክ ክልል የሚያስመጣ ወይም እንዲገባ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡
2) ***"ላኪ"*** ማለት ማናቸውም ዕቃ ከጉምሩክ ክልል የሚያስወጣ ወይም እንዲወጣ የሚያደርግ ሰው ነው፡፡
3) ***"ቀሪ ቀረጥና ታክስ "*** ማለት ወደ ሀገር ስገባ ወይም ከሀገር ስወጣ ዕቃ ሲከፈል ሲገባው ሳይከፈል የቀረ የቀረጥና ታክስ ዕዳ ነው፡፡

4) *"የውሳኔ ማስታወቂያ"* ማለት በምርመራ የተገኘ ቀረጥና ታክስና ሌሎች ክፍያዎችን እንዲከፈል ለባለዕዳው የሚሰጥ በፅሁፍ የተዘጋጀ ማስታወቂያ ነው፡፡

5) *"ዕዳ"* ማለት ለባለስልጣን መ/ቤቱ በወቅቱ መከፈል ሲገባው ያልተከፈለ ቀረጥና ታክስ /ወይም ወለድ ነው፡፡

6) *"የቀሪ ቀረጥና ታክስ ወለድ"* ማለት የቀሪ ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ቅድመ ክፍያ በመክፈል ቀሪ ቀረጥና ታክሱን በክፍያ ጊዜ ስምምነት ለመክፈል ሲስማማ ባልተከፈለው መጠን በባንክ የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ መሠረት የሚከፈል የገንዘብ ዕዳ ነው፡፡

7) *"ቅድመ ክፍያ"* ማለት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ለመክፈል በልዩነት እንዲከፍል ከተጠየቀው ከጠቅላላው ክፍያ ውስጥ ባለዕዳው በመጀመሪያ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡

8) *"ንብረት"* ማለት ቋሚ እና/ወይም ተንቀሳቃሽ ንብረትን እንዲሁም በባንክ የሚገኝ ገንዘብን ያካተተ ሀብት ነው፡፡

9) *"ቀሪ ክፍያ" ማለት ባለዕዳው እንዲከፍል ከተጠየቀው ቀሪ ቀረጥና ታክስ ቅድሚያ ክፍያ ከከፈለ በኋላ የሚኖረው ዕዳ እና ወለድ ነው፡፡*

10) *"ባለዕዳ "* ማለት ቀሪ ቀረጥና ታክስ የመክፈል ግዴታ በህግ የተጣለበት ሰው ነው፡፡

11) *"የቀሪ ክፍያ ጊዜ ስምምነት"* ማለት ባለዕዳው የተጠየቀውን የቀሪ ቀረጥና/ታክስ ክፍያ ግዴታውን በአንድ ጊዜ አጠናቆ መክፈል ሳይገደድ በዚህ መመሪያ በሚወሰን ጊዜና ሁኔታ ዕዳውን አጠናቆ እንዲከፍል የሚደረግበት ሥርዓት ነው ፡፡

12) *"ሀራጅ/ጨረታ"* ማለት የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ግዴታን ባለመወጣት የተያዘን ንብረት በግልጽ ወይም በዝግ ጨረታ የመሸጥ ሥነ-ስርዓት ሂደት ነው፡፡

13) *"አዋጅ"* ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው፡፡

14) በዚህ መመሪያ የተካተቱት ሌሎች ቃላትና ሐረጐች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ፡፡

## 3. የመመሪያው የተፈፃሚነት ወሰን

1) ይህ መመሪያ በድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ግኝት ወይም ያለኦዲት በሚገኝ/በሚጠየቅ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ እና ከዚህ ጋር በተያያዘ ግዴታ ባለባቸው ሰዎች ሳይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምባቸው፣ በኮንትሮባንድ፣ በቀረጥ ነፃ ወይም በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች የተሳለፈላቸው ሦስተኛ ወገኖች ወይም ተሽከርካሪዎች በቅን ልቦና በያዙ ሰዎች ሳይ የዚህ መመሪያ የቀሪ ሂሳብ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት አፈጻጸም

## 4. የውሳኔ ማስታወቂያ ስለመስጠት

1) በድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ወይም ለመንግስት መከፈል የነበረበት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ከተገኘ የቀሪ ሂሳቡን የገንዘብ መጠን የሚገልፅ የውሳኔ ማስታወቂያ ለባለዕዳው /ወኪል/ በጽሑፍ እንዲደርሰው መደረግ አለበት፡፡

2) ባለዕዳው በልዩነት የተጠየቀውን የቀረ ቀረጥና ታክስ ክፍያ ወዲያውኑ መክፈል የማይችል ከሆነ እና በጊዜ ገደብ ለመክፈል ከተስማማ ቅድሚያ ክፍያውን ከፍሎ በሚቀረው ላይ ተከፍሎ እስካለቀ ድረስ ወለድ የሚታሰብበት ይሆናል፡፡

3) የወለዱ መጠን በወቅቱ ባለው የንግድ ባንኮች የማበደሪያ የወለድ ምጣኔ መሠረት ይሆናል፡፡

## 5. ቅሬታ ወይም አቤቱታ ስለማቅረብ

1) በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ግኝት ቅሬታ ያለው ባለዕዳ የውሳኔ ማስታወቂያ ሲደርሰው ቅሬታውን ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡

2) ማንኛውም ኦዲት ተደራጊ አስመጪ/ላኪ በኦዲት ግኝት ባለዕዳ የሆነ ሰው በሪፖርቱ መሠረት የተጠየቀው የቀረጥና ታክስ ልዩነት ቀሪ ሒሳብ ላይ ቅሬታ ካለው የውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በጽሑፍ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ካላቀረበ የተጠየቀውን የልዩነት ክፍያ እንደተቀበለው ይቆጠራል፡፡

3) የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ጉዳዮን በመመርመር በ10 (አስር) ቀናት ውስጥ ለቅሬታ አቅራቢው ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ባለዕዳ በአዋጁ አንቀፅ 87 እና የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ቡድን ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 45/2002 መሠረት ቅሬታውን ለጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 6. የቀሪ ቀረጥና ታክስ አሰባሰብ

1) በኦዲት ልዩነት የተገኘውን ቀሪ ቀረጥና ታክስ የገቢ አሰባሰብ እና ዋስትና ሂሳቦች አያያዝ ቡድን በሚያቀርበው የውሳኔ አስተያየት መሠረት በቅ/ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ ውሳኔ በማሰጠት ተከታትሎ ያስከፍላል/ይሰበስባል፡፡

2) የገቢ አሰባሰብ የሥራ ሂደት በውሳኔ መሠረት ቀርቦ ክፍያ ያልፈፀመ ባለዕዳ ዝርዝር በመያዝ የንብረት መያዝ ህጉ ተፈፃሚ እንዲደረግበት ይህንኑ ለማስፈፀም ለተቋቋመው የሥራ ሂደት ያስተላልፋል፡፡

## 7. *የንብረት እና/ወይም ሀብት መያዝ*

1) የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለዕዳ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ዕዳውን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ አለበት፡፡ ይህን በማይፈፅም ሳይ የንብረት መያዝ ሥርዓት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2) በውሳኔው ማስታወቂያ ላይ ቅሬታ ያለው ባለዕዳ ውሳኔው በደረሰው 15 (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ ይችላል፡፡

3) የተያዘው ንብረት እስኪሸጥ ድረስ ለዚህ ተግባር ተብሎ በተቋቋመው ማቆያ /ማከማቻ/ ቦታ ጥበቃ እየተደረገለት ይቀመጣል፡፡

4) የተያዘው ንብረት /ሀብት/ ከተያዘበት ቀን አንስቶ በሚቆጠር 10 (አስር) የሥራ ቀናት በኋላ በሐራጅ መሸጥ ይቻላል፡፡

5) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ድንጋጌ ቢኖርም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በታየው ጊዜ ባለሥልጣኑ ሊሸጠው ይችላል፡፡

## 8. *ግዴታን አለመፈፀም*

1) ለኦዲት ስራ ሲባል የድርጅቱን የሂሳብ መዛግብት፣ የጉምሩክ ዲክላራሲዮኖችን፣ የግዥና ሽያጭ ሰነዶች በአጠቃላይ የገቢና ወጪ ንግድ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችንና መረጃዎችን እስከ 10 (አስር) ዓመት ድረስ ጠብቆ ያልያዘ/ያላቆየ፤
2) ተፈላጊ መዛግብትንና መረጃዎችን በኦዲተሮች ተጠይቆ ያላቀረበ ወይም ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆነ፣
3) የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲተሮች በሕግ በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የሚያከናውኑትን ስራ ያሰናከለና ጣልቃ በመግባት የኦዲት ሥራውን በተገቢው እንዳይከናወን ያደረገ፣
4) ለኦዲት ሥራ ሲባል በህጉ መሠረት ተፈላጊ ሰነዶችን ወይም የዕቃ ናሙናዎችን ለኦዲተሮች ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው በአዋጁ በተደነገገው መሠረት የፍትሐብሄር እና/ወይም የወንጀል ሃላፊነት ይኖርበታል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የቀሪ ቀረጥና ታክስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት

## 9. የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች

ይህ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

1. በልዩነት የሚፈለግ የቀረጥና ታክስ ክፍያ እንዲከፈል የውሳኔ ማስታወቂያ በደረሳቸው ባለዕዳዎች፤
2. ሳልተከፈለ የቀረጥና ታክስ ዕዳ ለማዋል ንብረታቸው ለተያዘባቸው ወይም ንብረታቸውን ለመሸጥ ሀራጅ ከወጣ በኋላ ለመክፈል ፈቃደኛ ለሆኑ ባለዕዳዎች፤
3. ህግን በመተላለፍ የተያዙ ተሽከርካሪዎች እና ቀረጥና ታክስ የሚፈለግባቸው ባለዕዳዎች፤

   ሀ. ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ሲኖርባቸው የቻለው አስቀድሞ መብት እንዳላቸው በማሰብ ወይም የቀረጥና ታክስ ዕዳ ያለመኖሩን ለማረጋገጥ ጥረት ሳደረጉ ባለዕዳዎች፣ ወይም

   ለ. የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት ወይም ከቀረጥና ታክስ ነፃ ወደ አገር ገብቶ ከሕግ ውጪ ወደ ሶስተኛ ወገን የተላለፈ ዕቃ ወይም ተሽከርካሪ ሲሆን፣ ወይም

   ሐ. የጉምሩክን ሕግ በመተላለፍ የገባን ዕቃ ወይም ተሽከርካሪ በሕግ የተሰጠውን የባለቤትነት ማስረጃ መሰረት አድርጎ ባለቤት ለመሆን አስቦ በቅን ልቦና ይዞ የተገኘ ሰው በሚሆንበት ጊዜ፣

   ለዕቃው ወይም ለተሽከርካሪው ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ፣ በአንድ ጊዜ ከፍሎ ዕቃው ወይም ተሽከርካሪውን ማስለቀቅ በማይችልበት ሁኔታ ቅድሚያ ክፍያ 25 %( ሃያ አምስት በመቶ) ከፍሎ ቀሪውን ክፍያ በሁለት ዓመት ጊዜ ለማጠናቀቅ ስምምነት ማድረግ ይችላል፡፡

## 10. የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት የማይፈቀድባቸው ሁኔታዎች

ማንኛውም ቀረጥና ታክስ በልዩነት የሚፈለግበት ባለዕዳ፣

1) ቀደም ሲል የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተሰጠው ሆኖ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታውን ሳይወጣ ከቀረ፣
2) ለአንድ የታክስና ቀረጥ የውሳኔ ማስታወቂያ ከአንድ ጊዜ በላይ የክፍያ ጊዜ ስምምነት የጠየቀ ከሆነ፣

3) የክፍያ ጊዜ ስምምነት የተጠየቀበት የዕዳ መጠን በዚህ መመሪያ ከተቀመጠው አነስተኛ የገንዘብ መጠን በታች ከሆነ፣

4) ለሁለት ጊዜ የጉምሩክ ቀረጥና/ታክስ ማጭበርበር የፈፀመ መሆኑ የኋላ ታሪክ የሚያስረዳ ከሆነ ወደፊት በማጭበርበር ተግባር ተሰማርቶ እንደማይገኝ ማረጋገጥ እስኪቻል ድረስ የክፍያ ጊዜ ስምምነት አይሰጠውም፡፡

## *11. የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄ አቀራረብ እና አፈፃፀም ሥርዓት*

1) የክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ጥያቄን የገቢ አሰባሰብብና የዋስትና ሂሳቦች የስራ ሂደት ተከታትሎ ተፈፃሚ ያደርጋል፡፡

2) ስሥራው አግባብነት ያለው የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሳቦች ቡድን ሰራተኛ የክፍያ ጊዜ ስምምነት ጥያቄ ይቀበላል፡፡ መርምሮ የስምምነት ውል በማዘጋጀት ለሥራ ሂደቱ መሪ ያቀርባል፡፡ የስራ ሂደቱ የውሳኔ አስተያየት በማዘጋጀት/በማቅረብ በቅ/ጽ/ቤቱ ስራ አስኪያጅ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

3) በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ተሰጥቷቸው ግዴታቸውን ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መወጣት ያልቻሉ ማስረጃ ሲያቀርቡ አግባብነት ያለው ሠራተኛ ጉዳዩን መርምሮ ለሥራ ሂደት ባለቤት ያቀርባል፡፡ የስራ ሂደት ባለቤት ጉዳዩን በተገቢው አጣርቶ ከውሳኔ ሃሳብ ጋር ለቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ያቀርብና ጊዜው እንዲራዘም ሲፈቅድ ይችላል፡፡

4) የክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል በ3 ኮፒ ተዘጋጅቶ ዋናው ኮፒ ከአስመጪው/ላኪው ዲክላራሲዮን ጋር ይያያዛል 2ኛው ለአስመጪው/ላኪው ይሰጣል 3ኛ ኮፒ ለክትትልና አፈፃፀም የሥራ ሂደት ይተላለፋል፡፡

## *12. ለክፍያ ጊዜ ማራዘሚያ ስምምነት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች*

1) በዚህ መመሪያ መሠረት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ለሚደረግ ቀረጥና ታክስ ዕዳዎች ቢያንስ 25% /ሃያ አምስት በመቶ/ በቅድሚያ ክፍያ ተፈፅሞ ቀሪው ዕዳ ክፍያ እንዲፈፅሙ ስምምነት ለሚገባባቸው ቀሪ ወራቶች እኩል ተካፍሎ ክፍያው የሚፈፀም ይሆናል፡፡

2) የክፍያ ስምምነት ጥያቄ የቀረበው የባለዕዳው ንብረት ወይም ሀብት ከተያዘ በኋላ ከሆነ ባለሥልጣኑ ጉዳዩን ለማስፈፀም ያወጣቸውን ወጪዎች እና በቅድሚያ ቢያንስ የቀረጥና ታክስ

ዕዳውን 50% ከከፈለ ቀሪውን ዕዳ በተቀመጠው የክፍያ ጊዜ ገደብ ውስጥ ክፍያው እንዲጠናቀቅ ስምምነት ይሰጠዋል፡፡

3) ጉዳዩ በፍርድ ቤት ወይም በፍርድ አፈፃፀም ላይ የሚገኝ ከሆነ ባለዕዳው ባለሥልጣኑ የቀረጥና ታክስ አሰባሰቡን አፈፃፀም ለመከታተል ያወጣቸውን ወጪዎች በሙሉ እንደ አግባብነቱ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ወይም /2/ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ጋር በቅድሚያ መክፈል ይኖርበታል፡፡

4) ቅድሚያ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ያሉት ቀሪ ክፍያዎች ላይ ስምምነቱ የሚታሰበውና የሚገባው ቅድሚያ ክፍያው ከተፈፀመበት ዕለት ጀምሮ ይሆናል፡፡

5) የክፍያ ስምምነት ጥያቄ የቀረበው የባለዕዳው ንብረት ወይም ሀብት ከተያዘ በኋላ ከሆነ በቅድሚያ በ50 % ( ሃምሳ በመቶ)፤ ንብረት ወይም ሀብት ከመያዙ በፊት ከሆነ 25 % (ሃያ አምስት በመቶ) በመክፈል ለቀሪው ዕዳ የዋስትና ቦንድ ማቅረብ የቻሉ ስምምነቱ እንዲፈፀም ለማድረግ ይችላል፡፡

## *13. የቀሪ ክፍያ ስምምነት የጊዜ ገደብ*

1. በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 በተመለከተ በልዩነት የሚከፈል የቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለዕዳ ጠቅላላ በልዩነት የሚፈለግበት ቀሪ ክፍያ እና ወለድ ከዚህ በታች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ይከፍላል፡፡

   ሀ. ከብር 50,000 /ሃምሳ ሺ/ እስከ 300,000 /ሦስት መቶ ሺ/ ከሆነ እስከ 6 ወር

   ለ. ከብር 300,001 /ሦስት መቶ ሺ አንድ/ እስከ 1,000.000 /አንድ ሚሊዮን/ ከሆነ እስከ 8 ወር

   ሐ. ከብር 1,000,001 /አንድ ሚሊዮን አንድ/ እስከ 1,500.000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ) ከሆነ እስከ 10 ወር

   መ. ከብር 1,500 001 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ አንድ) እና ከዛ በላይ ከሆነ እስከ 12 ወር ድረስ የክፍያ ጊዜ ገደብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ 3 የተገለጹት በተመለከተ 24 ወራት የክፍያ ጊዜ ገደብ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 14. *ልዩ ሁኔታ*

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ የሚወክለው ኃላፊ በልዩ ሁኔታ የተሰጠውን የክፍያ ጊዜ ሊያራዝም ይችላል፡፡

## 15. *ልዩ ልዩ ጉዳዮች*

1) በክፍያ ጊዜ ስምምነት ውል መሠረት ክፍያ የሚፈፀምበት ቀን በሕዝብ በዓላት ወይም ከሥራ ቀናት ውጭ ከዋለ ክፍያው በቀጣዩ የስራ ቀን መፈፀም አለበት፡፡
2) ስዚህ መመሪያ አፈፃፀም ጳጉሜ የነሐሴ ወር አካል ሆኖ ይቆጠራል፡፡
3) የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሳቦች የሥራ ሂደት እንዲሁም የደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት የክፍያ ጊዜ ስምምነት ስፈፀሙ አስመጪዎች/ላኪዎች ዝርዝር መረጃ ማለትም የክፍያ ስምምነት የተፈፀመበት የዲ/ዮን ቁጥርና ቀን፣ በልዩነት የተጠየቀ ቀረጥና ታክስ መቀጫ እና ወለድ በቅድሚያ የተከፈለ ገንዘብ መጠን ስምምነት የተፈፀመበት ቀን እና የመክፈያ ጊዜ ያካተተ ሪፖርት በየወሩ አያዘጋጀ ስሚመለከተው የዋና መ/ቤት ዳይሬክቶሬት ይልካል፡፡

## 16. *ግዴታን አለመፈፀም*

በዚህ መመሪያ በተሰጠው የክፍያ ጊዜ ስምምነት መሠረት በየወሩ ወይም በስምምነቱ በተገለፀው የአከፋፈል ሁኔታ እዳውን የማይከፍል ወይም መክፈል ያቋረጠ አስመጪና ወይም ላኪ ወይም ሌላ ሰው ያለ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያ የክፍያ ጊዜ ስምምነቱ ተቋርጦ ቀጣይ የቀረጥና ወይም ታክስ አሰባሰብ ሥነ-ሥርዓት ተፈፃሚ ይደረግበታል፡፡

# *ምዕራፍ አራት*

# *ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች*

## 17. *የመሸጋገሪያ ድንጋጌ*

ማንኛውም ባለዕዳ በዚህ መመሪያ የተጠየቁትን ቅድመ ሁኔታዎች ካሟላ ከዚህ መመሪያ መውጣት አስቀድሞ ሳለበትም ዕዳ የአከፋፈል ስምምነት ውል ማድረግ ይችላል፡፡

## 18. መመሪያው የሚፀናበት ቀን

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ………….ቀን 2004**

**መላኩ ፈንታ**
**የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን**
**ዋና ዳይሬክተር**